# ማኔ ቴቄል ፋሬስ

አማላይ ቃላቶች ፤ እየተናገረ
በትንሽ ትልቁ ፤ እንዳልተፈቀረ
በየ አደባባዩ ፤ እንዳልተሞሸረ
ከፍ ከፍ ፤ ተደርጎ ፤ ክብሩ እንዳልጨመረ
ከሰሜን ተራራ ፤ ገዝፎ እንዳልነበረ
ስሙ ፤ ካፅናፍ አፅናፍ ፤ እንዳልተዘመረ
አፈር መላሽ ሆኖ ፤ ወርቅ ላበደረ
አንድ ዓመት ሳይሞላው ፤ ሁሉም ተቀየረ
  በነበረ ብቻ ፤ ታሪክ ሆኖ ቀረ
  ማኔ ቴቄል ፋሬስ ፤ ሆኖ ተሰፈረ ፡፡

በኢትዮጵያ አምላክ ፤ መጣ የተቀባ
ብለን ተቀብለን ፤ በሆይታ ጭብጨባ
ሲተነፍስ ኖሮ ፤ በኦነጎች ሳንባ
ማንነቱን ጋርዶን ፤ ሸፍኗት በካባ
ባስገራሚ ፍጥነት ፤ ከዘውጉ ሲገባ
  ፍሬ ያፈራል ያልነው ፤ ሆነና ገለባ
  ያስለቀሰው ጀመር ፤ ሕዝቡን የደም ዕንባ ፡፡

ድንቅ ቃል ተናግሮ ፤ ልብን አማላዩ
ግብሩ ተንኮለኛ ፤ ባፉ ግን ሸንጋዩ
ዳግማዊ ብልጣሶር ፤ ትዕቢተኛ ዕቡዩ
ፈጣሪም እንዳለው ፤ የምድር የሰማዩ
  እንደተነገረው ፤ ዳንኤል ነብዩ
  ማኔ ቴቄል ፋሬስ ፤ ዛሬም ለአብዩ ፡፡

ስልጣን እንዳይመልስ ፤ ወደባለቤቱ
ከንቱ የሚመካው ፤ በሃይል በጉልበቱ
ይሄ ጎጥ አምላኩ ፤ ቄሮ ሰራዊቱ
የደንቆሮ ግምት ፤ ሆነና ስሌቱ
እየመጣ ያለው ፤ አደጋው ከፊቱ
ለመማር ተስኖት ፤ ካለፈው ከጥንቱ
  ዘርጥጠው ካልጣሉት ፤ ከስር መሰረቱ
  ከፉኛ ደንድኗልን ፤ ልቡ በትዕቢቱ ፡፡

ሰንደቁን አዋርዶ ፤ እምነትን የሚያረክስ
ተዋህዶን ገዳይ ፤ ኢትዮጵያን የሚያፈርስ
የመከራ ልዑክ ፤ የዲያቢሎስ ፈረስ
ወንድማማቾችን ፤ አናካሽ ፤ እርስ በርስ
  አውቆ እንዳላወቀ ፤ ግፍ መከራ ሲነግስ
  ናላው ስለዞረ ፤ በከንቱ መወደስ
  ዜጋም ይናገራል ፤ ማኔ ቴቄል ፋሬስ ፡፡

ታዛቢው

October 12, 2019